# ኔልሰን ማንዴላና ህፀፆቹ

**ጋዜጠኛ መስፍን አብርሃ/ጀርመን**



የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንትና የገዢው የኤኤንሲ /የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ/ፓርቲ ሊቀመንበር የነበሩትን ኔልሰን ሮሊህላህላ ማንዴላ ከሦስት ትውልድ ያላነሰ አፍሪካዊና የሌላው አህጉር ህዝብ ጠንቅቆ ያውቃቸዋል። እኚህ ሰው ይበልጥ ከሚታወቁባቸው ጉዳያቸው ውስጥ በአገሪቱ በነበረው አፓርታይድና ዘረኛ ስርዓት ለ27 ዓመታት መታሰራቸው ብሎም ከእስር በኋላ ለአሳሪዎቻቸውና በብዙ ሚሊዮን ጥቁር ደቡብ

Madiba-photo by Thierry Ehrmann/France

አፍሪካውያንን አንገብግበው ለገዙ የዘር መድሎ ለፈፀሙ እንዲሁም የግርፋት የግድያና የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን ለሰሩ ነጭ በዝባዡቻቸው ይቅር ማለታቸው ዋነኛው ነው።

ይህ ተግባራቸው በተለይ በመንፈሳዊ ህይወታቸው ከፍተኛ ይቅር ባይነታቸውን በስጋዊ ህይወታቸው ደግሞ በቀልን ያስወገዱበት በመሆኑ የዓለም አቀፉን የኖቤል የሰላም ሽልማት ከቀድሞው የአፓርታይዱ የመጨረሻ ዘመን ፕሬዚዳንትና በእሳቸው የፕሬዚዳንትነት ዘመን ምክትላቸው ከነበሩት ፍርድሪክ ዴክለርክ ጋር እ.ኤ.አ በ1993 አሸንፈዋል።

አንድ ክፍለ-ዘመን ሊሞላቸው 5 ዓመታት ብቻ የቀራቸው ማንዴላ በአገሬው አጠራር "ማዲባ" አባታችን ማለት ነው፣ ከማይቀረው ሞት ሊያመልጡ አልቻሉምና በስጋ ከተለዩን 3 ወራትን አስቆጥረዋል።

ሆኖም በዛሬው ርዕሴ የማዲባን በጎ ተግባራትና መንፈሳዊ ተጋድሎ ለመተረክ አልሞከርም።እንደው በደፈናው ማንዴላ የበቁ ቅዱስ ሰው ናቸው እንከንም የማይገኝባቸው ብለው ለሚሞግቱ ጸሐፍትና አማኞች ያላያችሁት ህፀፅ አላቸው፤ሰው መሆናቸውንም አትርሱ ለማለት ነው ብዕሬን የሳልኩት።በእርግጥ እንዲህ አይነት ጽሑፎች ለንባብ ሲበቁ ደስ የማይሰኙ ይኖራሉ።ቢሆንም እውነታን መጋፈጥ ጭፍን ደጋፊ ወይም ጭፍን ተቃዋሚ መሆንን ማስወገድ ስለሚገባን የማዲባን ህፀፅ ማየት ይገባናል።አንባብያን እንድትረዱልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር እኔም ማዲባን እወዳቸዋለሁ።መልካም ጎኖቻቸውንም አደንቃለሁ።ማዲባ ታላቅ ጀግና ናቸው።ግን ደግሞ የራሳቸውም ህፀፅ አለባቸው።

ኔልሰን ማንዴላን ማንሳቴ ስለ ኔልሰን ማንዴላ ብቻ ላወራ እንዳልሆነም አብዛኞቻችሁ ትረዱልኝ ይሆናል።አንድን ሰው ልክ እንደ መልዓክ አድርጎ መቁጠር ሰውየው ካለበት ችግር ሌላው እንዳይማር ይጋርዳል።ስህተቱንም የሚጠቁም ሰው ሲገኝ እንደ ጠላት ፀረ-አገርና ትውልድ ተደርጎ በአገራችንም ጭምር መታሰቡ እንዲቀር ስለሚያሳይ ነው።እንኳንስ የኛዎቹ መሪዎች/በተቃዋሚውም በመንግስትም ያሉት/ይቅርና ዓለም ስንት የደሰኮረላቸው ማንዴላም ህፀፅ ያለባቸው ሰው እንደነበሩ ለማሳየት መሞከሬ በእሳቸው ውስጥ ሌሎቹን የእኛ ሰዎች ለማየት ስለሚረዳ ነው።

ዛሬ ብዕሬ ማንዴላ ላይ አነጣጥራለች።ዓላማዋ ግን የእኛን ሰዎች በማንዴላ ውስጥ ማሳየት ይሆናል።ታላቁ መሪያችን አይሳሳቱም።ዶክተሩ ፕሮፌሰሩ ካሉ እንደ ወረደ መቀበል ነው እንጂ እሳቸውን የሚሞግት ሰው ደንቆሮ ነው ተብሎ የሚወረወሩት ጉንጭ አልፋ ክርክሮች ለማንም አይበጁምና ያለችን አንድ አገር ስለሆነች ብንደማመጥ እንደሚበጅ ለመጠቆም፤የአይን ክፋቱ ወደ ውስጥ ማየት አይችልምና በውጭ በኩል ያለውን ማንዴላን አርቀን በማማተር ውስጣችንን እንድንፈትሽ በማንዴላ ላይ ወደማተኮሩ ልመለስ።

ሌሎች ፀሐፍት ሌላ ሊሉ ይችላሉ እኔ ግን ማንዴላ የገዛ የአገራቸውን ህዝብ ከኢኮኖሚ ባርነት ያላወጡ በዚህም ጎዶሎ ያላቸው መሪ ነበሩ ብዬ አምናለሁ።ዛሬ ጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ምንም እንኳን ጥቁር መሪ ቢኖራቸውም እንደቀድሞው ፖለቲካዊ ነፃነት ባይነፈጋቸውም አሁንም ድረስ 2 በመቶ በማይሞሉት ነጮች የኢኮኖሚ አገዛዝ ስር ነው የሚኖሩት በሌላ አነጋገር **የኢኮኖሚ አፓርታይድ ስርዓት** በደቡብ አፍሪካ አልተገረሰሰም።

ደቡብ አፍሪካውያን በሆኑት ነጮች ጥቁሮችና ባለ ሌላ ቀለሞች ዜጎች መካከል ያለውን የገቢና የኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር ሁኔታ ለማየት የሚከተለውን ሰንጠረዥ ማየት ይጠቅማል።"R``የሚለው የደቡብ አፍሪካ የመገበያያ ገንዘብ ራንድ

የሚባለውን የሚወክል ሲሆን አንድ የአሜሪካን ዶላር በወቅቱ በ4.6 ራንድ ይመነዘራል።ዛሬ ምንዛሪው ወደ 11 ራንድ ደርሷል።

ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው የነፍስ ወከፍ ገቢ የ30 ዓመታትን የገቢ መረጃ የያዘ ሲሆን በተለይ በአፓርታይዱ ዘመን የነበረውን የከፋ ሁኔታ በግልፅ ለመረዳት ይጠቅማል።ከአፓርታይዱ አገዛዝ ወዲህም ለውጡ ላለው ይጨመርለታል ነውና ብሂሉ ነጮቹ ገቢያቸው እጅግ ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ጨምሯል።የጥቁሮቹም ጨምሯል ግን ለውጡ እዚህ ግባ የማይባል ነው።

| Per capita income 70 | | 75 | 80 | 85 | 90 | 95 | 2000 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Blacks | R 3 134 | R 4 479 | R 5 107 | R 5 423 | R 6 008 | R 6 704 | R 7 283 |
| Coloureds | R 8 184 | R 8 630 | R 8 822 | R 9 855 | R 11 404 | R 12 722 | R 14 126 |
| Indians | R 9 595 | R 11 244 | R 13 296 | R 15 113 | R 17 637 | R 20 592 | R 23 938 |
| Whites | R 39 217 | R 44 242 | R 46 670 | R 48 370 | R 51 951 | R 53 840 | R 62 360 |
| Total | R 9 936 | R 11 626 | R 12 125 | R 12 385 | R 12 903 | R 13 436 | R 14 716 |

**Source: Van der Berg & Louw 2004, using estimates derived from a variety of sources**

የማዲባን የፕሬዚዳንትነት ዘመን ብናይ ደግሞ ከ1995-2000 ያለውን ማለት ነው የሚከተለውን ይመስላል።

| Per capita income | 95 | 2000 |
|---|---|---|
| **Blacks** | R 6 704 | R 7 283 |
| **colored's** | R 12 722 | R 14 126 |
| **Indians** | R 20 592 | R 23 938 |
| **Whites** | R 53 840 | R 62 360 |
| **Total** | R 13 436 | **R 14716** |

**Mandela`s presidency years**

ከሰንጠረዡ የምንረዳው በማዲባ ፕሬዚዳንትነት ዘመን የጥቁሮቹ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአንድ ሺ ራንድ ሲያድግ የነጮቹ በ9ሺ ራንድ አድጓል። በአፓርታይዱ ዘመን በተደረገ ጥናት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 56 በመቶ ጥቁሮች 27 በመቶ ባለሌላ ቀለሞች 9 በመቶ ህንዶችና 2 በመቶ ነጮች ነበሩ።ይኸው የአፖአርታይድ ጠባሳ ኢኤአ በ1994 አፓርታይዱ ከተገረሰሰ በኋላም በዜጎቹ መሃል ከፍተኛ የሆነ የገቢ ልዩነት አምጥቷል። ገዢው ANC '' የጥቁሮችን ኢኮኖሚ ማጎልበት"ወይም በእንግሊዘኛው ምህፃረ-ቃል BEE- /Black Economic Empowerment / የሚል ፕሮግራም ነድፎ መንቀሳቀስ ቢጀምርም ከግቡ ሳያደርሰው እንደው እንደ አገራችን "የውሃ ማቆር ቴክኖሎጂ" የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል።በዚህም ምክንያት ያለፈው የ2013 የአገሪቱን የስራ አጥ ቁጥር ብናየው ከአገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ 25.2 በመቶው ስራ አጥ ነው። ምናልባትም ይሄ ቁጥር ለእንደኛ አይነት አገር ታዲያ ምን ችግር አለው?ጥሩ ነው ሊባል ይችላል። ከተጠቀሰው ቁጥር ውስጥ የጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ድርሻ ቢለካ ግማሽ ሰው ስለሌለ ነው እንጂ ከ8ቱ ሰዎች አንዱ ነው ስራ ያለው። እሱም እዚህ ግባ የሚባል ስራ ማለት ነው።ስራ ስንል ማንኛውንም ስራ ትንሽም ቢሆን ገቢ ያለውን ነው። ለዚህም ነው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የዘረፋ ወንጀል እንደ ስራ መቆጠር የተጀመረው። በደቡብ አፍሪካ እንደኛ አገር 50 በመቶ በእርሻ የሚተዳደር አርሷደር የለም። ከአጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እርሻ የሚሸፍነው 2.6 በመቶ ብቻ ነው።እንደ CIA world fact book ከሆነ *Agriculture: 2.6%፤Industry: 28.4% services: 69% (2012 est.) ነው የአገሪቱን ኢኮኖሚ የያዘው።

- ታዲያ ማንዴላን የሚያስወቅሳቸው ብዬ የማምንበት ትልቁ ነጥብ በእሳቸው የፕሬዚዳንትነት ዘመን አንደኛ በመጠኑም ቢሆን 2 በመቶ የማይሆኑት ነጮች ከያዟቸው የቢዝነስ ኩባንያዎች የእርሻ ለም መሬቶችና የአገልግሎት ተቋማት 50 በመቶ የሚሆኑትን እንደ መታረቂያ እንዲሆን ወደ መንግስት ይዞታነት ተለውጠው ጥቁሮች አቅማቸውን የሚያዳብሩበትን፣ በኩራት በአገራቸው በድህነታቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የማይታዩበትን ሁኔታ መፍጠር ሲችሉ አልተጠቀሙበትም።

- በሁለተኛ ደረጃ ገዢው ፓርቲ ኤኤንሲ ያወጣውን ፕሮግራም ጥርሳቸውን ነክሰው በማስፈፀም የመሰረት ድንጋዩን ቢጥሉ ኖሮ ተከታዮቻቸውም ይህንኑ በመከተል ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ እየሰፋ ያለውን የዜጎች የገቢ ልዩነት ማጥበብ ይቻል ነበር። ማዲባ ይህን ማድረግ ባለመቻላቸው የጥቁር ደቡብ አፍሪካውያንን የተሟላ ነፃነት ማሟላት ተስኗቸው ቀርቷል።

- በሦስተኛ ደረጃ በእኔ አይታ የነጭ ባለሃብቶችን የኩባንያዎች አክሲዮን ድርሻ ቢያንስ 40 በመቶ ለጥቁሮች እንዲሸጡ በማድረግ ከገቢው የጋራ ተቋዳሾች እንዲሆኑ ማድረግ ሲቻል ሳይሆን

> ቀርቷል።ጥቁሮቹ በየትኛው አቅማቸው የአክሲዮን ሼሮችን መግዛት ይችላሉ ቢባል መንግስት የብድር እድሎችን በማመቻቸት እንዲሁም ጋን በጠጠር ይደገፋል እንደሚባለው በርካቶች የአቅማቸውን ሼር በመግዛት ማስተካከል የሚቻል ግን ያልተሳኩ ወይም ያልታሰቡ ህፀፆች ሆነዋል በማዲባ ዘመን።

ሌላው ቢቀር ማዲባ ከፕሬዚዳንትነታቸው ከወረዱ በኋላም ቢሆን ያላቸውን ተሰሚነት በመጠቀም የአገሪቱን ጥቁር ህዝቦች ከኢኮኖሚ ባርነት ለማላቀቅ ጥረት ማድረግ ነበረባቸው።ይህ አልሆነም።ስለዚህ አብዛኞቹ ጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ሀብታም የሚባሉት በፓርላማ የተመረጡ ባለስልጣናት የምግብና የመጠጥ ቤቶች ባለቤቶች ናቸው እንጂ የትላልቅ ኩባንያዎች ባለቤቶች ሲሆኑ አይታይም።የተወሰኑ አሉ ግን ቁጥራቸው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

ደቡብ አፍሪካ በኢኮኖሚ አቅሟ ጂ5 ወይም BRICS (Brazil, Russia, India, China, South Africa) የሚባሉት በማደግ ላይ የሚገኙ አገራት ተርታ ተሰልፋ አህጉረ አፍሪካን ወክላ የምትገኝ አገር ናት።አገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚ የምታንቀሳቅስ በመሆኗም በአፍሪካ ግንባር ቀደም ለመሆን በቅታለች።ግን በጥቋቁር መሪዎች ስር ያለችው ደቡብ አፍሪካ ጥቁር ዜጎቿን በኢኮኖሚ ዘርፍ ከባርነት ልታወጣቸው እስካሁን አልቻለችም።እድሉ ግን አሁንም የተዘጋ አይደለም።

የዓለምአቀፉ መገናኛ ብዙኀን የማዲባን ችግሮች ከመዘገብ ይልቅ የዚምባብዌውን ፕሬዚዳንት ሮበርት ሙጋቤን ማብጠልጠላቸውን እንደቀጠሉበት ነው። የነጮቹን ጥቅም የነኩት ከማዲባ ይልቅ ሙጋቤ ናቸውና።ሙጋቤ በዓለማችን አምባገነኖች ዝርዝር ውስጥ ከተካተቱ ውለው አድረዋል።ለዘመናት ስልጣን የሙጥኝ ብለው እሳቸውም አበዙት ለዘመናት አንድ ፊት ማየትም እኮ ይሰለቻል።ነገር ግን የአገሪቱን ጥቁር ህዝቦች የሃብታቸው ተጠቃሚ ለማድረግ የወሰዱት እርምጃ(በነጮች ተይዘው የነበሩ የአገሪቱ 70 በመቶ ለም መሬቶችን ለድሃ አርሷደሮች ማከፋፈላቸው) ግብታዊነት የተሞላበት ሆነና ትንሽ ተበላሸባቸው እንጂ በመሰረቱ ተገቢ ነው።በተለይ በዘዴ ቢያደርጉት ደግሞ እጅግ በጣም የተሳካ ይሆን ነበር።

ማንዴላ በዘዴ በብስለትና ከፍተኛ በሆነ የመደራደር አቅማቸው ከሙጋቤ የተሻሉ ሰው ነበሩ ብዬ ስለማምን ዘዴውን ተጠቅመውበት ቢሆን ኖሮ ህዝባቸውን ከኢኮኖሚ ባርነትም ነፃ አውጥተው አቻችለው ያልፉ ነበር።ያ እንኳን ባይሆን ቢበዛ የሙጋቤ እጣ ፈንታ ነበር የሚደርስባቸው።ሙጋቤ ህዝባቸውን በመካሳቸው ምንም እንኳን በምዕራባውያኑ የማይወደዱ ቢሆንም ለህዝባቸው ግን አዲስ ታሪካዊ ምዕራፍን ከፍተዋል።ምን ያህል ዴሞክራሲያዊ እንደሆነ መገመት ቢቸግርም በህዝባቸው ይሁንታን አግኝተው ወይም የብዙኀኑ ህዝባዊ አመፅ ሳይነሳባቸው ለዘመናት ስልጣናቸውን እንደተቆናጠጡ ይገኛሉ።

ስለዚህ ምዕራባውያኑም ሆኑ የእኛን መሰሎቹ በማዲባ ሌጋሲ ውስጥ የእኛም አስተዋፅኦ ነበረበት ለማለት የሚችሉትን ብለዋል።በሙጋቤ እርምጃ የተነሳ በዚምባብዌ ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ሲጣል ግን የአፍሪካ መንግስታት ትንፍሽ አላሉም።ጌቶቻቸውን እንዳያስቆጡ ማለት ነው።

ደቡብ አፍሪካውያን ጥቁሮች አሁንም በመጤዎቹ ዜጎች የኢኮኖሚ የበላይነት ወይም በኢኮኖሚ አፓርታይድ ውስጥ ይገኛሉ።ለዚህ ደግሞ የመልካም ስራቸውን ያህል በእኔ እምነት ማንዴላ ከሚወቀሱበት አንዱና ዋነኛው ህፀፅ ወይም ችግራቸው ነው።

እርግጥ ነው ዛሬ ዛሬ በደቡብ አፍሪካ በነጮቹ ኩባንያዎች ስር የሚተዳደሩት ጥቁሮች በሚያገኙት ክፍያና በመሳሰሉት ነገሮች ተቃውሞአቸውን ማሰማት ጀምረዋል። አመጽም ሲያቀጣጥሉ ማስተዋል ጀምረናል።ይህ ነገር ኤኤንሲን የፖሊሲ ለውጥ እንዲያደርግ ያስገድደው ይሆን?ከርመን የምናየው ይሆናል።

እኛ ግን በተለይ ኢትዮጵያውያን የወደድነውን ሰው ሁሉ በግድ እንዲወድልን የጠላነውን በግድ በጅምላ እንዲጠላልን ማሰብ ማቆም ይኖርብናል።የእኔን ሃሳብ በግድ ዋጡ ማለት አምባገነንነት ነው።ስለሆነም ለተለየ ሃሳብ አክብሮት ሊኖረን ይገባል።አንድ ሰው ወይም ተቋም በአንድ ጉዳይ ላይ እንደ አሻራችን የተለየ ሃሳብ ቢያንፀባርቅ ሃሳቡን ለመረዳት እንሞክር።ጆሮ ሰጥተን እናድምጥና በሃሳቡ ዙሪያ መከራከሪያችንን እናቅርብ እንጂ ይሄ የእንትና ደጋፊ ነው ተቃዋሚ ነው የእንትና ዘር ስለሆነ ነው እያልን በጅምላ አንፈርጅ።እንኳንስ እኛ ማንዴላም የግዙፍ ህፀፅ ባለቤት ነውና!ቸር እንሰንብት።